በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ 203538

ህዳር 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አቶ ሳቢት አባ ዲንካ- ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጣሂር አባ ዲንካ- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በቀን 26/06/2013 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የሲግሞ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 34088 በቀን 20/06/2013 ዓ.ም፣ የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 54191 በቀን 25/03/2013 ዓ.ም፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 224595 በቀን 22/04/2013 ዓ.ም እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 334929 በቀን 20/05/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው። ክርክሩ የውረስ ይዞታ መሬትን የተመለከተ ሲሆን የጀመረው በወረዳ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች በቀን 25/03/2012 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ እናቴ ወ/ሮ አቶሜ አባፎጊ በቀን 20/02/1991 ዓ.ም በሞት ተለይታለች፤ የሟች ወራሽ የሆነው ልጆች ከሳሽና ተከሳሽ ብቻ ነን፤ እናታችን ትታው ያለፈችው በሁለት ቦታ የሚገኝ ይዞታ ሲሆን በ1ኛው ቦታ ስፋቱ 20 በ 80 የሆነ አዋሳኙ በክሱ የተገለፀው እና በግምት 2000.00 ብር የሚያወጣ ባህር ዛፍ፤ እንዲሁም 2ኛው ቦታ ስፋቱ 20 በ 30 የሆነ አዋሳኙ በክሱ የተገለፀው የሚገኝ ሲሆን ተከሳሽ የውርስ ድርሻየን ከህግ ውጪ ይዞ ስለከለከለኝ ድርሻየን ግማሹን እንዲያካፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት እናታችን ከሞተች 20 አመት ስለሆነ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል ካሉ በኋላ በፍሬ ነገር መልሳቸው ደግሞ 1ኛው ቦታ 20 በ 80 የሆነውና ባህርዛፍ እንዲሁም 2ኛው ቦታ 20 በ30 የሆነው ይዞታ የውርስ መሬት ሳይሆን የግል ይዞታዬ ነው፤ አባቴ በህይወት በነበረ ጊዜ የሰጠኝ ነው፤ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ በይዞታው እየተጠቀምኩበት ስለሆነ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በ1ኛ ቦታ ያለው መሬት በሚመለከት ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው፤ በ2ኛ ቦታ ላይ ያለው መሬት በተመለከተ የግራ ቀኙ ምስክሮች በተመሳሳይ ቃል የመሬት ይዞታው የውርስ መሆኑን አረጋግጠዋል፤ ተከሳሽ ይህ መሬት ይዞታ አባቴ በህይወት በነበረ ግዜ በስጦታ የሰጠኝ ነው ከማለት ውጭ በሚያሳምን ሁኔታ ተቀባይነት ባለው መልኩ አባቱ መስጠቱን የሚያሳይ እንዲሁም የግሉ መሆኑን የሚያስረዳ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር፣ የግብር ደረሰኝ ወይም መሬቱ በስሙ መኖሩን እና መጠቀሙን የሚያሳይ ማስረጃ አልተገኘም፤ አከራካሪውን ይዞታ ሲጠቀሙበት የነበሩበት ስለሆነ ወራሾች ለመውረስ መብት ያላቸው በመሆኑ 2ተኛውን የመሬት ይዞታ እኩል እንዲካፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እንዲሁም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ቢያቀርቡም ቀባይነት አላገኙም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት ማመልከቻ የስር ወረዳ ፍ/ቤት ከአከራካሪው 2ኛ ቦታ 20 በ30 በእኩል እንድንካፈል ወስኖልኝ 1ኛው ቦታ 20 በ 80 የሆነውን ተጠሪ ያለአንዳች ምክንያት ከነድርሻዬ ጭምር ይዞ እያለ ተጠሪ በ3 አመት ይርጋ ክሱ ቀሪ ይሆናል ስላለ ብቻ

ፍ/ቤቱ በአግባቡ ሳያጣራ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው ምክንያቱም ይዞታውን እስከ 2011 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር አብረን ስንጠቀም ስለቆየን ከይርጋ ጋር አይገናኝም፤ ተጠሪ ታናሼ በመሆኑ ቤተሰቦቼ ለእኔ ትተው በመሞታቸው አብረን እስከ 2011 ዓ.ም ስንጠቀም ቆይተን በ2011 ዓ.ም ሁከት ፈጥሮብኝ ተጋጭተን ከዛ በኋላ መሬቱን ፈቅደን ወደን ለመከፋፈል አሰብን እንጂ የተጠሪ የግል ይዞታ አይደለም፡፡ አባቴ አከራካሪውን 20 በ 80 የሆነ ይዞታ በስጦታ ለተጠሪ አልሰጠም እንጂ ቢሰጥም ህጋዊ የስጦታ ፎርማሊቲ ያላሟላ እና በገጠር መሬት አዋጅ 133/98 አንቀጽ 23/4 መሰረት እና ሰበር በመ/ቁ 115399 በሰጠው ትርጉም መሰረት አግባብ ባለው አካል ያልተመዘገበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ ተጠሪ አባቱ በህይወት እያለ በስጦታ መሰጠቱን እያመነ እና ምስክሮችም በስጦታ ከአባቱ እንደተላለፈ እየመሰከሩለት በ1ኛው በታ ድርሻውን ተካፍሎ በ2ኛው በታ 20 በ 80 የሆነውን ከ20 አመት በፊት ተላፎልኛል የሚለው ሚዛናዊነት የሌለው በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ተሽሮ ሁሉንም በታ በጋራ እንድንካፈል ይወሰንልኝ በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የክርክር መነሻ የሆነውና ተጠቅሶ የቀረበው 20 በ80 ሜትር ይዞታ በግራ ቀኙ መካከል ሳይካፈል የታለፈበት አግባብነት ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ባቀረቡት መልስ የስር ፍ/ቤቶች የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ያደረጉበት መነሻ ተጠሪ ያቀረብኩትን የመጀመሪያ ደረጃ የይርጋ መቃወሚያ መሰረት በማድረግ ሲሆን መቃወሚያውም የውርስ ጥያቄው እናታችን ከሞተች 20 አመት ካለፈው በኋላ የቀረበ በመሆኑ እና አከራካሪውን ንብረት አመልካች በተጠሪ መያዙን ካወቀ ከ3 አመት በላይ ካለፈ በኋላ የቀረበ በመሆኑ ነው፡፡ አመልካች እናታችን በቀን 20/02/1991 ዓ.ም እንደሞተች በግልጽ ያስቀመጠው ሲሆን አቤቱታውን ያቀረበው ደግሞ በቀን 25/03/12 ዓ.ም ነው፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ይዞታውን በእጄ አድርጌ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ስገለገልበት 25 አመት ያለፈኝ መሆኑን ያቀረብኳቸው ምስክሮች በሚገባ ያስረዱ ከመሆኑም በተጨማሪ የአመልካች ምስክሮችም ይዞታውን አመልካች የውርስ ጥያቄ ከማቅረቡ በፊት ለረጅም ግዜ ስገለገልበት የነበርኩ መሆኑን መስክረዋል፡፡ አመልካች በአቤቱታው ይዞታውን እስከ 2011 ዓ.ም አብረን ስንጠቀም ነበር በሚል ያቀረበው ከእውነት የራቀ ሲሆን ተጠሪ ለብቻዬ ስገለገልበት የቆየ

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

መሆኑን በስር ፍ/ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አቤቱታው እናታችን ከሞቱ 20 አመት በኋላ የቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1000 መሰረት የቀረበው የውርስ ጥያቄ በማንኛውም አስተያየት ተቀባይነት የለውም፡፡ አመልካች በመብቱ ተጠቅሞ የውርስ ጥያቄ እንዳያቀርብ በህግ ፊት ተቀባይነት ያለው ምክንያት የነበረው ስለመሆኑ ማስረዳትም አልቻለም፤ እንዲሁም ይርጋው ከመቆጠር መቋረጥ የሚያስችል ምክንያት የነበረ ስለመሆኑም በስር ፍ/ቤት የቀረበ መከራከሪያ የለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በአመልካች የቀረበው የውርስ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሰጠው ውሳኔ ምንም አይነት የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ ውሳኔው እንዲጸና በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በመልስ መልሳቸው አቤቱታቸውን በማጠናከር አቅርበዋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀው ከውርስ ሃብት ጋር በተያያዘ ወራሽ ነኝ የሚል ወገን መብቱንና የውርስ ንብረቶቹ በሌላ ወራሽ መያዛቸውን ካወቀ ከሶስት ዓመት በኃላ የሚያቀርበው የወራሽነት ክስ ተቀባይነት እንደማይኖረው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1000(1) ስር ተመልክቷል፡፡ ይህን የይርጋ ድንጋጌ አስመልክቶ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 26422 እና 20295 እንዲሁም በሌሎች በርካታ መዛግብት አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በሌላም በኩል በመጀመሪያው ፍርድ ቤት ያልተነሳውን ክርክና ያልቀረበውን አዲስ ነገር ይግባኝ ሰሚው (የበላይ) ፍርድ ቤት ለመቀበል አይችልም፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በስር ፍርድ ቤት እናታቸው ወ/ሮ አቶሜ አባፎጊ በቀን 20/02/1991 ዓ.ም መሞታቸውን ገልፀው ለወራሾች ሊተላለፍ የሚገባውን ሁለት በታ ላይ ያለ ይዞታና ባህር ዛፍ ድርሻቸውን ተጠሪ እንዲያካፍላቸው የጠየቁት በቀን 25/03/2012 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው በግልፅ ክሱ በይርጋ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ክርክሩ በወራሾች መካከል በመሆኑና ክሱ የቀረበው አውራሽ ከሞቱ ከ 20 ዓመት በኃላ በመሆኑ ይርጋ መቆጠር የሚቋረጥበት ምክንያት ስለመኖሩ ክርክርና ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ ክሱ ከፍሲል በተጠቀሰው የህግ አግባብ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ነው፡፡

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

አመልካች በውርስ ይዞታው እስከ 2011 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር አብረን ስንጠቀም ቆይተናል በማለት በዚህ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቢገልፁም ይህን ክርክራቸውን በስር ፍርድ ቤት ማቅረባቸውን መዝገቡ አያሳይም፡፡ በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳው ክርክር በዚህ ፍርድ ቤት የሚቀርብበትና ተቀባይነት የሚያገኝነት የህግ አግባብ አግባብ የለም፡፡

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት በ1ኛው ቦታ ያለውን መሬት በሚመለከት ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ብሎ 2ተኛውን የመሬት ይዞታ እኩል እንዲካፈሉ በማለት ውሳኔ መስጠቱ አመልካችን የጠቀመ ነው ከሚባል በቀር ከአመልካች አንጻር ውሳኔው የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የሲግሞ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 34088 በቀን 20/06/2013 ዓ.ም፣ የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 54191 በቀን 25/03/2013 ዓ.ም፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 224595 በቀን 22/04/2013 ዓ.ም እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 334929 በቀን 20/05/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. እግድ ካለ ተነስቷል፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማ/አ　　　　　　　　　　የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም